# የጀልባዋ ጉዞ

**/ ገለታው ከሣር ቤት /**

ከወዲያ ማዶ የሕፃናት ሰቆቃና የጣር ድምፅ ይሰማል፡፡ አረጋውያን ጧሪ አጥተው ቀሪውን የህይወት ዘመናቸውን እንዴት እንደሚገፉት በሐሳብ ቆዝመዋል፡፡ ወጣቶች ተስፋቸው ተሟጥጦ በኑሮ ጣዕም ትርጉም ግራ ተጋብተዋል፡፡ ዜጎች መቋጫ በሌለው ረሀብና ስደት መንገላታት፤ እርስ በርስ በሚጠፋፉበት ግጭት ዘወትር ግራ መጋባት፤ ከጎረቤቶች ጭምር መተረማመስ፤ ሠላምን ነፍጎ ሠላምን ማጣት፡፡ ታዲያ እነዚህን ሁሉ ለመታደግ ነበር የጀልባዋ በውቅያኖሱ ዳርቻ ላይ የመገኘቷ ሚስጥር፡፡

ፀሐይዋ ከእነ ልጆቿ የወጣች ይመስል የአንዳንዱ ቀን ሰማይ በሙቀትና ብርሃን ተሞልቶ ወገግ እንዳለ ነግቶ ይመሻል፡፡ ሲለው ነጎድጓዳማ ኃይለኛ ድምጽ እያሰማ ውቅያኖሱን መጣሁ… ደረስኩ እያለ ያሸብረዋል፡፡ መብረቅ ሰማዩን ለሁለት ከፍሎ ውቅያኖሱን ከዳር እስከ ዳር በብርሃን ይሞላዋል፡፡ ይኼኔ ጨገግ ያለው ምሽት በብርሃን ተተክቶ ብዙም ሣይቆይ ሥፍራውን ለጨለማ ይለቃል - ድቅድቅ ያለ ጨለማ፡፡ ለነገሩ ሊነጋጋ ሲል አይደል ጨለማውስ የሚብሰው፡፡

እንዲህ …  እንዲህ እያለ ይነጋል፣ ይመሻል፡፡ ቀናት በሣምንታት፣ በወራት፣ ወራት በዓመታት እየተተካኩ የጊዜ ሽክርክሪት ዑደቱን ጠብቆ መጓዙን አያቋርጥም፡፡ ይኼ ሁሉ ሲሆን ጀልባዋ ከሁለት እጅ ጣቶች ያነሱ ተሣፋሪዎችን ይዛ ጉዞዋን አሀዱ ብላ ጀምራለች - በወርሃ የካቲት፡፡

ጀልባዋ ለመድረሻዋ ረዥም ውስብስብ ጉዞ ይጠብቃታል፡፡ ፀጥ ባለው በዚህ ሰፊ ውቅያኖስ ጉዞው ላይጎረብጣት፣ አቅጣጫዋን ላትስት፣ በባህር ውስጥ ላትሰምጥ፣ በአውሎ ነፋስ ላትመታ - ላትዋዥቅ፣ በውሽንፍር ላትናጥ ምን ዋስትና አላት? ብቻ እንዲያም ሆኖ ጀልባዋ ጉዞዋን ቀጥላለች፡፡

ረዥሙ ጉዞ አሰልቺና አድካሚ እንደሚሆን ተሳፋሪዎቹ ገና ከመነሻው ያጡት አይመስልም፡፡ ለዚያም ቢሆን ተሰናድተዋል፤ በአጭሩ ታጥቀዋል፡፡ ረሀብና ጥማቱ ሌላው ችግር ሊሆን እንደሚችልም ታሳቢ አድርገዋል፡፡

ከውቅያኖሱ አንደኛው አቅጣጫ ሣይታሰብ የተነሳው ኃይለኛ ማዕበል ጀልባዋን ከወዲያ ወዲህ ይንጣታል፤ ከአንዱ ዳር አንስቶ ከሌላው ጥግ ያላትማታል፡፡ ያኔም በተሳፋሪዎቿ ዘንድ ሽብር ሰፍኗል፤ ሥጋት ተቀስቅሷል፡፡ የዳር ተመልካቾች "አሁንስ ይህች ጀልባ አበቃላት፤ አከተመላት" ብለው መጥፎ ተንብየውላታል፤ ተሳልቀውባታልም፡፡

ይሁንና ጀልባዋን ከዚህ ጭንቅ ለማውጣት ሁሉም ተሳፋሪዎች አቅማቸውን አሟጥጠው ተፍጨርጭረዋል፡፡ ከብዙ ውጣ ውረድ፣ ውጥረትና ትንቅንቅ በኋላም ተሳክቶላቸው ጀልባዋን ከተጋረጠባት የመስመጥ አደጋ ታድገዋታል፡፡ ጀልባዋም የጀመረችውን ጉዞ እንደገና ቀጥላለች፡፡

ጀልባዋ አሁን አዳዲስ ተሳፋሪዎችን ጨምራለች፡፡ ምሉዕ እምነት ይዛለች፡፡ በሁሉም ዘንድ መረጋጋት ሰፍኗል፡፡ ጉዞውም ቀጥሏል፡፡ ከፊት ለፊቷ ከሚጠብቃት ቀውስ ለማዳን ብሎም ከተጋረጠባት መደናቅፍ ለማትረፍ አዲስ ስልት ተነድፎላታል፡፡

በጉዞው አስቸጋሪነት የተፈተኑ፣ በአድካሚነቱ የተሰላቹ፣ ተስፋ የቆረጡ፣ መጪው ብሩህ ተስፋ አልታይ ብሏቸው ፈተናውን የወደቁ፣ የተቸነከሩ፣ ለአፍቃሪ ነዋይ የተንበረከኩ፣ እጅ አንስተው የሰጡ ከውቅያኖሱ መሀል ሰጥመዋል፡፡ ጥቂት  የማይባሉትም በየደሴቶቹ ተንጠባጥበው ቀርተዋል፡፡ ጀልባዋ ያራገፈቻቸውንና የጣለቻቸውን ትታ አዳዲስ ተሞሻሪዎችን ጨምራ ጉዞዋን ቀጥላለች፡፡

ከፈጣኑ ሂደት ጋር ራሳቸውን አዋህደው ሊዘልቁ ያልቻሉ፤ በአካልም ሆነ በመንፈስ በፅናት ጠንክረው ያልወጡ፤ በጉዞው ተዳክመው የተሰናከሉ ከውቅያኖሱ ዳርቻዎች ተተፍተውና፣ ተሽቀንጥረው ወድቀው ቀርተዋል፡፡ ጥቂት የማይባሉ ተሳፋሪዎች በአቋማቸው እንደፀኑ ለመከራና ፈተና ሳይንበረከኩ እስከ ወዲያኛው አሽልበዋል፡፡ በርካቶች በሰማዕታቱ እግር ተተክተው የጉዞው አካል ሆነው ሂደቱን ለማቀጣጠል ተቀላቅለዋል፡፡

ለአዲስ ህይወት ማበብ ተስፋ የሰነቁ፣ የተሻለ ጊዜን የሚጠብቁ፣ ለእስትንፋሻቸው መቀጠል በጀልባዋ ላይ እምነት የጣሉ ሚሊዮኖች ሂደቱን በንቃት ይከታተላሉ፡፡ ጀልባዋም መድረሻዋን እየናፈቀች በጉዞዋ ላይ ነች፡፡

በዚህ ረዥም የውቅያኖስ ላይ ጉዞ ክፉ ደጉ ታይቷል፡፡ ምን … ምን ችግሮች ተከሰቱ? የትኞቹ ጋሬጣዎች የባሱ አደጋዎች ነበሩ? እንዴትስ ታለፉ? በጋራ ተመክሮባቸዋል፡፡ ቀጣዩ ጉዞ እንዴት ይሁን? ይኼም ተፈትሿል፡፡ የሁሉም ተሳፋሪ ሀሳብ በግልፅነት ይደመጣል፡፡ የተሻለው ተይዞ ጉዞው ይቀጥላል፡፡

ጀልባዋ በእስከዛሬው የውቅያኖስ ላይ ቆይታዋ በርካቶች ተፈራርቀው መዘውሯን ይዘዋል፡፡ እገሌ ብቻ ካልሆነ ተብሎ አይፈረጅም፡፡ ከተሳፋሪዎች መካከል ብቃትና ክህሎቱን ያለው እስከተወሰነ ርቀት የጀልባዋን መዘውር ጨብጦ ይጓዛል፡፡ ነገ ለሌላ ለባለተራው ወጣት ያስረክባል፡፡ ባለተራውም መጓዝ እስካለበት ሄዶ የመሪነቱን መዘውር ለሌላ አሳልፎ ይሰጣል፡፡ አንዱ ጀምሮ ለሌላው፣ ይኼ ለዚያኛው፣ ያኛው ለዚህኛው - የቅብብሎሽ ሩጫ፡፡ የቅብብሎሽ ሩጫ በአንድ ሰው ተጀምሮ በዚያ ሰው ብቻ መጠናቀቅ ግድ ከሚለው የማራቶን ሩጫ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡

“የነገው የጀልባዋ ዘዋሪ ማን ይሁን?” ለሚለው ተሳፈሪዎቿ ከወዲሁ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎችን እየከወኑ ነው፡፡ ነባሩ ዘዋሪ ልምድና እውቀቱን ለተተኪው የሚያጋራበት እድልም ተፈጥሮለታል፡፡ ሁኔታዎችም ተመቻችተውለታል፡፡ “ቅብብሎሽ” ማለት ይኸው ነው፡፡ መዘወሩን ለመጨበጥ ጦር መሳበቅና ጐራዴ መማዘዝ በዚህች ጀልባ ላይ አይሰራም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ልማድም የላትም፡፡ ይኼ ሁሉ ሲሆን ጀልባዋ አሁንም መስመሯን ጠብቃ ይዛ በጉዞዋ ላይ ናት፡፡ ሚሊዮኖችን ከጐኗ አሳፍራ ለሚሊዮኖች ትሩፋት ለመሆን ፍጥነቷን ጨምራለች፡፡

አሁን ብዙዎች ኑሮን ማጣጣም ይዘዋል፤ ለነገ ብሩህ ተስፋን ሰንቀዋል፤ ሠላማዊ አየርን መማግ ጀምረዋል፤ በሠላም ወጥቶ ሰርቶ መግባት ተችሎበታል፤ አይሞከሬ የነበረው በነፃነት መንቀሳቀስ ዛሬ ያለከልካይ ተፈፅሟል፡፡ ለበለጠ የህይወት ሥምረት ጀልባዋ በጉዞዋ ላይ ናት ፡፡

ዛሬ ጀልባዋ ባለተራ ዘዋሪዋን ከተሳፋሪዎቿ ጋር አጣምራ ጉዞዋን ቀጥላለች፡፡ የሁሉንም ሠላምና ፍቅር ይዛ ለዜጐች የተሻለ ህይወት ሲባል አሁንም በጉዞዋ ላይ ናት፡፡

ወደ ኋላ ጐታቾች፣ ዳተኞች፣ ጠባቂዎች፣ ጨለምተኞች፣ ክፉ አሳቢዎች፣ ሟርተኞች ዛሬም እንደያኔው በዚያችው ሥፍራ በሐሜት ጀልባዎቻቸው ላይ ቆመው እንዳላገጡ አሉ፡፡ ወደፊት አይጓዙ አሊያም አይሰምጡ፡፡ ሠላም፡፡